ሰምና ወርቅ (ክፍል II)
BY: cosmos-2000, March 2009

ከውጭ የመጡት መነኩሴ
መች የሄዳሉ ቅድሴ
ከመንግሥት ጋር ሲውሉ
ቆባቸውን ያወልቃሉ::
ፍቅርማ ቢያስበልጡ
ዙሪያ ጠምጥመው አይመጡ::

የራሱን መሬት ተነጥቆ
ያነባል አሉ ተደብቆ::
ድሮ አያለቅስም ነበር
ቢጠናበት ነው ችግር::
አስለቃሽ ካለ ባገር
መግጠም አይቀር የምር::

ጠልቆ ይቆፈር እንደገና
ሚሠራው ሕንፃ እንዲ ፀና
ብረት ተረብርቦ በስሚንቶ
መሰረት ጣሉ ማዘን ቀርቶ::

የቂቤው መውጫ ከወተቱ
አልደረሰም ወይ ስዓቱ?
ይብቃ እንግዲህ መገፋቱ::

በሳንቃው ላይ ሰወች አሉ
ከሙታን ላይ የተሳሉ::
የተረሸኑት በሩምታ
ተረፈረፉ ባንዳፍታ::
ሰዎቹማ ይታወቃሉ
መለስና ሰይፉ ይባላሉ

የአልበሽርን መግለጫ
ለመለስ ሰጡት በሩጫ::
ሲነበብ መልክቱ
"የአርማጭሆ መዋጋቱ
ያርበኞቹ ብርታቱ
ካውደውጊያው የዋሉቱ
የሚሰዋው ላንድነቱ
ባይኖረው ነው ዕውቀቱ::
ተገንዝቦ ቢሆን ኖሮ
መሬት መዞሯን ተምሮ
አይዋጋም ነበር ጠንክሮ"::

ሃቀኞችን በግፍ ሲያስር
ወጀብ ላከ የሽብር
የነፋሱ አቅጣጫ ሲቀየር
አንድነት ለሚሹ በፍቅር
በረከት መውረዱ አይቀር::

ጥሩ ሽማኔ አገኘን

ጥበብ ሚሠራልን::
ገና ስም ስንጠራ ሰምቶ
ጥሎን ሄደ ተቆጥቶ::
እባክህ እነርሱን አትጥራ
ውብ ጥበብ እንዲሠራ::

የመከርናቸው ሲግሩ
ወያኔወቹ አስቸገሩ::
መሄዳቸውን ብናውቅ
ከማናያቸው ሩቅ
እንሰንቅ ነበር ስንቅ::
ይበሉት ብለህ ሲደርቅ
ዳቦ ቆሎ ነው ምናውቅ::
እንደውጭ እናርገው ብንል
የፈረንጆችን አይመስል
የማይሰነብት ባገልግል::
ያዘወትራሉ መውጣቱን
ካቭያር ለምደው እንደሆን::
ወትሮስ የለመደ የውጭ
ማን ያቆመዋል ቢሆን ነጭ?
እንኳን ነጭ ቢሁን ቢጫ
ወደ አኖሩበት ነው ሩጫ::

እንደጥንቱ እንደ አባት አደሩ
ወረርሽኝ ከገባ ባገሩ
ማስታገሻ የሚሆን መድሃኒት
ሂዱና አምጡ ወልቃይት::

ሰይጣናዊ ሥራ ጀምሮ
መሃሪነታችን ተነግሮ
ንስሃ እንዲገባ ተመክሮ
አሻፈረኝ ካለ አምርሮ
እንዲያው አይድንም ዘንድሮ::

ሱዳን አገኘ ሙሉ አገር
አንገቱን ደፋ ጎንደር::
መሬቱን ለሱዳን የሰጡቱ
ቀጥ ብሎ ሲያዩት ካንገቱ
አበሳጫቸው ቅናቱ::